# አብዮታዊ
# ዴሞክራሲ (ብአዴን)

(ቁጥር 006)

## ዜና

ኢህአዴግ

### ሁሉም ለምርጫው እንዲረባረብ ጥሪ አቀረበ

ኢህአዴግ በመጭው ሚያዝያ የሚካሄደው ምርጫ በተሳካ ሁኔታ እስኪጠናቀቅ ድረስ አባላቱ፣ ደጋፊዎቹና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ጥሪ አቀረበ።

የኢህአዴግ ምርጫ ኮሚቴ የበላይ አመራሮች አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝና አቶ ታደሰ ካሳ ሰሞኑን እንደገለፁት ምርጫውን ዴሞክራሲያዊ፣ ህጋዊና ሰላማዊ ለማድረግ ኢህአዴግ ከመቼውም ጊዜ በላይ ተዘጋጅቷል። የምርጫ ሂደቱም ያለ እንከን እንዲካሄድ ሁሉም የበኩሉን አስተዋፅኦ ማበርከት ይኖርበታል።

አባላቱ የኢህአዴግን የምርጫ ግቦች ተገንዝበው ለስኬታማነቱ የመንቀሳቀስ፣ ድርጅቱ ያዘጋጀውን የምርጫ ስነ ምግባር መሰረት በማድረግ ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎችን የማስረዳት፣ የመቀስቀስና የማነሳሳት፣ ምርጫው በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድ ሃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ የበላይ አመራሮች አስረድተዋል።

ደጋፊዎቹና ህዝቡም የተጀመሩትን የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎች ቀጣይነት እንዲኖራቸው የሚያደርጉና የሚታዩ ችግሮችን ሊፈቱ ይችላሉ የሚሏቸውን ወኪሎች ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ሊመርጡ እንደሚገባ ተናግረዋል። ለምርጫው ስኬታማነትም መረባረብ ይጠበቅባቸዋልም ብለዋል።

ምርጫው ዴሞክራሲያዊ፣ ህጋዊና ሰላማዊ እንዲሆንና የላቀ የህዝብ ተሳትፎ እንዲኖር ማድረግ፣ ፓርቲዎች በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ የሚወዳደሩበትን ሁኔታ መፍጠር ፣ ብቃት ያለው ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት የሚሉት የኢህአዴግ የምርጫ ዋነኛ ግቦች መሆናቸውን የበላይ አመራሮቹ ጠቁመዋል።

ኢህአዴግ እነዚህን ግቦች ለማሳካት እንቅስቃሴ መጀመሩን የገለፁት የበላይ አመራሮቹ ከማዕከል እስከ ቀበሌ ድረስ የምርጫ ኮሚቴዎችና ንኡሳን ኮሚቴዎች መዋቀራቸውን ገልፀዋል።

በህዝቡ ተቀባይነት ያላቸው፣ የማስፈፀም ብቃታቸው የተረጋገጠ፣ አርአያ የሆኑ አራት ሚሊዮን የሚጠጉ ዕጩዎችን አዘጋጅቶ ማቅረቡንና ዕጩዎቹንም በህዝብ የማስተቸት ስራ መጀመሩን ጠቅሰዋል።

በምርጫው ሁሉም ፓርቲዎች በንቃት ሊሳተፉ እንደሚገባ ኢህአዴግ ያምናል ያሉት የበላይ አመራሮቹ ህጋዊ መንገድ ብቻ ይዘው እንዲጓዙ ከህዝቡ ጋር ሆኖ እንደሚታገልም አስገንዝበዋል፡፡

ቁልፍ የሆነው የአስተዳደር ዕርከን የቀበሌና የወረዳ ምርጫ በመሆኑ ይህ ምርጫ ህዝቡ የኔ የሚለው ወኪሉን የሚመርጥበት ትልቅ እድል መሆኑንና ለስኬታማነቱ ሁሉም ሊረባረብ እንደሚገባ የኢህአዴግ የምርጫ ኮሚቴ የባለይ አመራሮች አስምረ ውበታል፡፡

# ዕጩዎችን ለማስተቸት የአመራሩ ሚና መጠናከር አለበት

## *ያልተመዘገቡ የመራጭነት ካርድ እንዲወስዱ ጥሪ ቀረበ

ዕጩዎችን በየደረጃው ማስገምገምና ማስተቸት፣ እንዲሁም አባላት በንቃት ተሳታፊ የሚሆኑበትን መንገድ መፍጠር በየደረጃው የሚገኝ አመራር ተግባር መሆኑን ብአዴን ገለፀ::

የብአዴን ጽ/ቤት እንዳስታወቀው ለአካባ ቢና ማሟያ ምርጫ የሚወዳደሩ ዕጩዎቹን ለይቶ የማዘጋጀት፣ የአባላትና የህዝብ መድረክ ከፍቶ ዕጩዎቹ እንዲተቹ ማድረግ በየደረጃው የሚገኘው አመራር አካል ድርሻ ነው::

የዕጩዎች ዝግጅትና ምልመላ በሁሉም ደረጃ እየተካሄደ ሲሆን እንደሰሜን ወሎ ዞን በመሳሰሉ አካባቢዎች አመራሩ ትኩረት ሰጥቶ በመስራቱ የተሻለ ክንውን መታየቱን ጽ/ቤቱ አስታውቋል::

በዞኑ እጩዎችን የማዘጋጀት ስራ ከአባላት ጀምሮ የተሳተፉበት ሲሆን፣ የህዝብ መድረክ በመክፈትም የማስተቸት ስራ መጀመ ሩን ጽ/ቤቱ ገልፆ፣ የሴቶችንና የወጣቶችን ተሳትፎ በተያዘለት እቅድ መሰረት ከ30 እስከ 40 በመቶ የማሳካት ተግባር መሆኑን አሳውቋል::

በክልሉ በሚገኙ ሌሎች ዞኖች በአንዳን ዶቹ የዕጩዎች ዝግጅትና የህዝብ መድረክ ከፍቶ የማስተቸት ስራ በመጀመር ላይ ሲሆን በአንዳንዶቹ ደግሞ ተግባሩ በተደራጀ መልክ እየተመራ እንዳልሆነ ጽ/ቤቱ ገልጿል::

የብአዴን ጽ/ቤት በየደረጃው ለሚገኙ አመራር አካላት ባስተላለፈው ጥሪ ዕጩዎችን የማዘጋጀት፣ በአባ ላት የማስተቸትና ለህዝብ መድረክ የማቅረቡ ስራ በተደራጀና በተጠናከረ መልኩ መቀጠል ይገባዋል ብሏል::

በቀጣዮቹ ጊዜያት ሶስት ተደጋጋፊና ተመጋጋቢ ስራዎችን አያይዘን መስራት ይገባ ናል ያለው የብአዴን ጽ/ቤት፣ የዕጩ ዝግጅትን በተመለከተ የሴቶችና ወጣቶች ተሳትፎን ማጠናከር፣ ዕጩዎቹ በአባላት ቀጥተኛ ተሳትፎ የተመረጡ መሆናቸውን ማረጋገጥና በተለይም በገጠር የተዘጋጁ ዕጩዎችን በህዝብ የማስተቸት ተግባር ፈጥኖ መተግበር እንደሚገባ አስታውቋል::

በየደረጃው የሚገኘው አመራር ተግባሩን ተከፋፍሎ የመምራት፣ መረጃ የመለዋወጥና ድጋፍ የመስጠት ስራውን በንቃት ሊገባበት እንደሚገባ ጽ/ቤቱ ገልጿል::

አባላት በዕጩዎች ምልመላና ዝግጅት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ከማድረግ ባሻገር፣ የተሳሳቱ ዝንባሌዎችና አመለካከቶችን በተለመደው ድርጅታዊ ባህልና ዲሲፕሊን ታግሎ ማስተካከል እንደሚያስፈልግ ጽ/ቤቱ ጥሪውን አስተላልፏል::

በሌላ በኩል የመራጭነትን መስፈርት ያሟሉት በየምርጫ ጣቢያው እየተመዘገቡ ካርድ እየወሰዱ መሆናቸውን ያሳወቀው ፅ/ቤቱ በቀሪዎቹ ጥቂት ቀናት ውስጥ በመመዝገብ መብታቸውን መጠቀም እንዳለባቸው ፅ/ቤቱ ጥሪውን አቅርቧል:: በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታየው ጊዜ አለ በሚል የመዘናጋት ሁኔታ ተወግዶ መላው መራጭ ህዝብ ካርዱን ለምርጫው ዝግጁ ሆኖ መገኘት እንደሚኖርበት የብአዴን ፅ/ቤት አሳስቧል:: ብአዴን ለአካባቢና ማሟያ ምርጫ አንድ ሚሊዮን 7ሺ 620 ዕጩዎችን ማቅረቡ ይታወቃል::

# የልማት ጀግኖቹ ሚዳሊያ ገና ያበራል!

**(ሪፖርታዥ)**

**ጥር 3 ቀን**

ሀዋሳ ከተማ ከወትሮው በተለየ ደምቃለች። ሁለተኛውን አገር አቀፍ የአርሶ አደሮች ፌስቲቫል ለመካፈል ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በተሰበሰቡ እንግዶቿ አሸብርቃ ነው የሰነበተችው። ከጥር 3 እስከ ጥር 7 የተካሄደው የአርሶ አደሮችና ከፊል አርሶ አደሮች አገር አቀፍ ፌስቲቫል በይፋ የተጀመረው በሀዋሳው መስቀል አደባባይ በተዘጋጀው ኤግዚቢሽን ነው።

በተለያዩ የሰብል አይነቶች፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች፣ የእደጥበብና የባልትና ውጤቶች የተዘጋጀው ኤግዚቢሽን በፌዴራል ፖሊስ ማርሽ ዜማ ነበር መከፈቱ የተበሰረው። የኤግዚቢሽኑ ታዳሚዎች በርካቶች ናቸው። የመንግስት ባለስልጣናት፣ የከተማዋ ነዋሪዎችና ተሸላሚ አርሶ አደሮች ተመልክተውታል።

**ጥር 4 ጠዋት**

ረፋዱ ላይ በሀዋሳው ሲዳማ ባህል አዳራሽ የልማት አርበኞች፣ ክቡራን ሚኒስትሮች፣ አምባሳደሮችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል። የልማት ጀግና አርሶ አደሮች በነጭ ኮፍያ፣ በነጭ ካናቴራና በአረንጓዴ ሪቫናቸው ደምቀዋል። ፊታቸው አንዳች የደስታና የድል አድራጊነት ፀዳል ይነበብበታል። ዛሬም እንደ ትናንቱ የፌዴራል ፖሊስ ማርሽ የበአሉን መከፈት በሙዚቃው አበሰረ። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በቦታው ሲደርሱም የልማት አርበኞቹ በህብረት ዝማሬዎቻቸው አቀባበል አደረጉ።

የበአሉ ጅማሬ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊና በደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽፈራው ሽጉጤ በተለኮሰው ሻማ አሀዱ ተባለ። ከዚያ በመቀጠል ደግሞ በባህል ዜማዎችና ውዝዋዜዎች የታጀበው የኪነት ቡድን ቀጠለ። የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስትር ህዝብ ግንኙነት ሃላፊ አቶ ታረቀኝ ፅጌም በመክፈቻ ንግግራቸው 676 ያህል የልማት አርበኞች በዕለቱ እንደሚሸለሙ ገለፁ። በዚህም 535 ያህል አርሶ አደሮችና ከፊል አርሶ አደሮች፣ እስከ 5 ሚሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ 30 የልማት ጀግና እማወራ አርሶ አደሮች፣ ባለሃብቶች፣ ብድርና ቁጠባ ማህበራት የልማት ጣቢያ ባለሙያዎችና አመራሮች የሽልማቱ ተቋዳሽ እንደሚሆኑ ተናግረው የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስትር አቶ አዲሱ ለገሰን ወደ መድረኩ ጋበዙ።

አቶ አዲሱ በንግግራቸው «በመጀመሪያው አገር አቀፍ የአርሶ አደሮች ፌስቲቫል ብዙዎች በ10ሺዎች ጥቂቶች ደግሞ በመቶ ሺዎች ያስቆጠራችሁ የልማት ጀግኖች ነበራችሁ። ዛሬ ደግሞ ብዙዎች በመቶ ሺዎችና ጥቂቶቹ ደግሞ በሚሊዮኖች ያስቆጠራችሁ፣ በድህነት ላይ ድልን የተቀዳጃችሁ፣ ግንባር ቀደም የልማት ጀግኖች ለሀገራችን ኩራት ናችሁ። የዛሬው ውጤት የተገኘው በጀግኖች አርሶ አደሮች ቢሆንም ከጀርባ ያላችሁ የልማት ጣቢያ ሰራተኞች፣ የህብረት ስራ ማህበራትና አመራሮች ለዚህ በመብቃታችን እንኳን ደስ አላችሁ።» ብለዋል።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊም «'የነብርን ጅራት አይዙም፤ ከያዙም አይለቁም'» እንደሚባለው የሀገራችን አርሶ አደሮች የልማትን ጅራት ይዘዋል፤ አይለቁምም። ለ5ኛ ጊዜ ለተደገመው

የልማት እድገት ባለቤት የሆናችሁ የልማት ጀግኖች የልማትን ጅራት ይዛችኋል፣ ሳትለቁ ለ6ኛ ጊዜ እድገት በማስመዝገብ ለ3ኛው ሀገር አቀፍ ሽልማት ለመብቃት የሚያስችል ብሩህ ተስፋ በእጃችሁ ነው፡፡» ነበር ያሉት፡፡

በመቀጠልም የልማት አርበኛ ተሸላሚዎች በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር የተዘጋጀላቸውን የክብር ሜዳሊያ አንድ በአንድ ማጥለቅ ጀመሩ፡፡ እዚህ ላይ የተለያዩ ስሜቶች ናቸው የተንፀባረቁት፡፡ ከፊሉ በደስታ ብዛት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀረብ ብሎ ሚስጢር ቢጤ ጣል ያደርጋል፤ ከፊሉ መድረክ ላይ ቆሞ የልማት ክንዶቹን ከፍ አድርጎ እጆቹን ያውለበልባል፤ ሌላው ደግሞ የተሰማውን ድምፁን ከፍ አድርጎ ይናገራል…፡፡ የልፋት ውጤት፣ የጥረት ዋጋ ምን ያህል የደስታ ሲቃ እንዳለው መገመት አያዳግትም፡፡

ከአማራ ክልል ደብረማርቆስ ዞን እናርጅ እናውጋ ወረዳ በከብት ማድለብ፣ በንብ ቀፎና በጓሮ አትክልት ልማት ውጤታማነት የተሸለመችው ወጣት አርሶ አደር አዳሚቱ ፀጋ በጠቅላይ ሚኒስትሩ እጅ ሜዳሊያ አጥልቃ ከመድረክ ስትወርድ «አሁን ውስጤ ትልቅ ጥንካሬ አለ፡፡ ጥረት በማድረግ ነው ለዚህ የበቃሁት፡፡ የቸኮልኩት ወደ አካባቢዬ ተመልሼ እጥፍ ሰርቼ ለሌላ ሽልማት ለመብቃትና ከኋላዬ በርካቶችን ለማስከተል ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ አሁንም መንግስት ከጎናችን እንደሚቆም እርግጠኛ ነኝ» አለችን፡፡

ሌላው ተሸላሚ ከደቡብ ክልል ኮንሶ ልዩ ወረዳ ከቡሶ ቀበሌ ገበሬ ማህበር የመጣ ነው፤ አርሶ አደር ኦቾ አያና «የምንኖርበት አካባቢ ወጣ ገባ የመሬት አቀማመጥ ያለበት ነው፡፡ እኛ በልፋታችን ውጤት በልማት ጀግና ተብለናል፡፡ ይሄ ትልቅ ነገር ነው፡፡ እኔ በአፈርና አካባቢ ጥበቃና በደን ልማት ነው የተሸለምኩት፡፡ ከ72 ሺ በላይ ችግኝ አፍልቼ 36ሺ ያህሉን ለአርሶ አደሩ አከፋፍያለሁ፡፡ ከአትክልትና ፍራፍሬ በአመት ከ10ሺ ብር በላይ ገቢ አገኛለሁ፡፡ እኔ ከዚህ የበለጠ ለመስራት ተነሳስቻለሁ፡፡» ነበር ያለው የልማት ጀግንነት ሜዳሊያውን አጥልቆ፡፡

ሽልማቱ ቀጥሏል፤ የልማት አርበኞቹ ሜዳሊያቸውን እያጠለቁ ነው፡፡ ለዚህ ውጤት ደግሞ በርካቶች ከጎናቸው ተሰልፈዋል፡፡ የወረዳና የቀበሌ አመራሮች፣ የህብረት ስራ ዩኒየኖች፣ የግብርና ባለሙያዎች …. እነሱም ላበረከቱት አስተዋፅኦ የሽልማቱ ተቋዳሾች ነበሩ፡፡

የኦሮሚያ ክልል ሉሜ አዳማ የገበሬዎች ዩኒየንም በዕለቱ ተሸላሚ ነበር፡፡ አቶ ደመረ ደምሴ የዩኒየኑ ዋና ስራ አስኪያጅ ናቸው፡፡ ዩኒየኑ አርሶ አደሩ ምርታማነቱን አሳድጎ ከዋጋ ተቀባይነት ወደ ዋጋ ሰጭነት እንዲሸጋገር ባደረገው አስተዋፅኦ ተሸላሚ እንደሆነ ነው የገለፁልን፡፡ ለዚህ ደግሞ ዩኒየኑ የተለያዩ ግብአቶችን ከማቅረብ ጀምሮ አርሶ አደሩ ተገቢውን ዋጋ እንዲያገኝ በማድረግና በብድርም ተጠቃሚ እንዲሆን በማገዝ ተንቀሳቅሷል፡፡ «ዩኒየኖች የራሱ የአርሶ አደሩ ድርጅቶች ናቸው፡፡ ለውጤቱ ጉልህ ድርሻ አበርክተዋል፡፡ ወደፊትም ብዙ ይጠበቅባቸዋል፡፡» ብለዋል፡፡

የደቡብ ጎንደሯ ሊቦ ከምከም ወረዳ በአካባቢው ከሚገኙ 11 ወረዳዎች መካከል በሞዴል ወረዳነትና በሞዴል አመራርነት ተሸላሚ ሆናለች፡፡ የወረዳዋ አስተዳዳሪ አቶ መንግስቴ አምሳሉ «የወረዳዋ ሞዴል አመራር ተብዬ ተሸላሚ ሆኛለሁ፡፡ በወረዳችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጥ አለ፡፡ በተለይ ደግሞ አምና የነበረው የአርሶ አደሮች ሽልማት ትልቅ የውድድር መንፈስ ነበር የፈጠረው፡፡ በውድድር መንፈስ መስራታችን ለውጤት አብቅቶናል» ብለዋል፡፡

ጥር 5 ቀን

ዛሬም በሲዳማ ባህል አዳራሽ የልማት አርበኞቹ ታድመዋል - የአካባቢውን የልማት ተመክሮ ለማድመጥና የልምድ ተሞክሮ ለመቅሰም፡፡ ከአማራ፣ ከትግራይ፣ ከኦሮሚያና ከደቡብ ክልሎች የተገኙ የግብርና ባለሙያዎች የልማት ስራው እንዴት እንደሚከወን፣ ምን ችግሮች እንደገጠሟቸውና እንዴት እየተወጡት እንደሆነ ልምዳቸውን እያቀረቡ ነው፡፡

በልምድ ተሞክሮ ልውውጡ ከታደሙት የልማት ጀግና አርሶ አደሮች ከአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን የጁቤ ወረዳ የመጣችው ጥሩ አለም ሃይሉ «እዚህ ብዙ ልምድ ቀስሜያለሁ፡፡ ቢ.ቢ.ኤም ያሉትን እኔም ሞክሬያለሁ፡፡ በጥቁር አፈር አጠንፍፌ ዘርቼ ጥሩ ምርት አግኝቻለሁ፡፡ ሌሎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችም ጥሩ ናቸው፡፡ ከገጠማቸው ችግርና አሁን ካገኙት ውጤት ትምህርት ቀስሜያለሁ፡፡ የተማርኩትን በአካባቢዬ ተግባራዊ ለማድረግ በውስጤ ይገፋፋኛል» ብላለች፡፡

ከኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን የመጣው አርሶ አደር ኑሬ ፋሪስም ከፓናል ውይይቱ ያገኘው ተመክሮ ቀሪ ነገሮችን ለማስተካከልና የበለጠ ውጤታማ ለመሆን እንደሚያግዘው ነው የገለፀው፡፡

ጥር 6 ቀን

እለተ ማክሰኞ ጠዋት በደቡብ ክልል የተመረጡ የልማት እንቅስቃሴዎችን ለልማት ጀግኖቹ ለማስጎብኘት ታቅዶ ነበርና ከሀዋሳ ከተማ በ96 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደምትገኘው አላባ ልዩ ወረዳ ጉዞ ተጀመረ፡፡ አላባዎች አቀባበላቸው ልዩ ነበር፡፡ በባህላዊ ዜማዎቻቸው ደምቀዋል፡፡ በዋነኛነት በበርበሬ ምርት የምትታወቀው አላባ አርሶ አደሮቿ የበርበሬ ምርትን በብዛት በማምረት ውጤት ያስመዘገቡባት ናት፡፡ በአካባቢው ከበርበሬ ምርት ከ300ሺ ብር በላይ በአንድ ጊዜ በማግኘት መኪና የገዙ፣ የተንጣለለ መኖሪያ ቤት በከተማ የገነቡ በርካቶች ናቸው፡፡

በጉብኝቱ ተካፋይ ከሆኑት አርሶ አደሮች መካከል ከአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን አምባሰል ወረዳ ማርዬ ቀበሌ የመጣው አርሶ አደር ፍሰሃ አዲሴ ከጉብኝቱ ብዙ ተመክሮ መቅሰሙን ገልጿል፡፡ «ከጉብኝቱ ብዙ ልምድ አግኝቻለሁ፡፡ በበርበሬ ምርትም ህይወታቸው ተቀይሯል፡፡ በርበሬ ከእኛ አካባቢ የአየር ፀባይ ጋር የሚሄድ በመሆኑ ይህንን ልምድ ተግባራዊ ለማድረግ አስቤያለሁ፡፡» ብሏል፡፡

የትግራይ ክልሉ የልማት ጀግና አርሶ አደር ራስ ገ/እግዚአብሄር አምሃም «አላባ ላይ የምርት አመራረትን ብቻ ሳይሆን ከተመረተ በኋላ በጥንቃቄ መያዝንም አይቻለሁ፡፡ እዚህ ያገኘሁትን ልምድ ለጎረቤቶቼ ለማካፈልም ዝግጁ ነኝ፡፡» ነበር ያሉት፡፡

በደቡብ ክልል ርዕሰ መዲና እንዲህ ደምቆ የሰነበተው ሁለተኛው አገር አቀፍ የአርሶ አደሮች ፌስቲቫል ከነድምቀቱ ተቋጭቷል፡፡ አምና በርካቶችን፣ ዘንድሮ ደግሞ እጅግ በርካቶችን የልማት ጀግኖች አፍርተናል፡፡ ወደፊት ደግሞ አእላፎችን እንደምናፈራ አመላክቷል፡፡ የልማት አርበኞቹ የቀራጥነት መንፈስ ደግሞ ገና ብዙ .... ብዙዎችን የልማት ጀግኖች እንደሚያስከትል በሽልማቱ መድረክ የተንፀባረቀው የአርሶ አደሮቹ መንፈስ፣ ስሜትና ደስታ እንዲሁም ቃል ምስክር ነው፡፡

# በመስኖ ከ22 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ይጠበቃል

በአማራ ክልል ዘንድሮ በመስኖ ከ22 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅ የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ አስታወቀ።

በቢሮው የመስኖ አግሮኖሚ ባለሙያ አቶ ሃብቴ ሆነልኝ ለጋዜጣው ሪፖርተር እንደገለፁት በዚህ አመት 325ሺ.500 ሄክታር መሬት በመስኖ በማልማት 22 ሚሊዮን 135ሺ.974 ኩንታል የተለያየ ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል።

በዚህም በክልሉ በሁሉም ወረዳዎች የሚገኙ ከአንድ ሚሊዮን 493ሺ. በላይ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ አቶ ሃብቴ ጠቁመዋል። ባለፈው አመት ከ1 ሚሊዮን 200ሺ. በላይ አርሶ አደሮች በመስኖ መሳተፋቸውንም አስታውሰዋል።

ዘንድሮ ይለማል ተብሎ ከታቀደው ውስጥ እስካሁን ከ108 ሺ. 800 በላይ ሄክታር መሬት ማልማት የተቻለ ሲሆን ይህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 17 በመቶ ብልጫ እንዳለው ባለሙያው ተናግረዋል።

ባለፈው አመት 318ሺ. ሄክታር መሬት በማልማት ከ19 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት መገኘቱን ያስታወሱት አቶ ሃብቴ የዘንድሮው ምርት ወደ 3 ሚሊዮን ኩንታል የሚጠጋ አብላጫ ምርት ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

በመስኖ የሚገኘው ምርት ሊጨምር የቻለው አርሶ አደሩ በመስኖ በስፋት እንዲጠቀምና በቴክኖሎጂዎቹ እውቀት እንዲኖረው ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራዎች በመሰራታቸው መሆኑን የተናገሩት ባለሙያው አርሶ አደሩ በአሁኑ ጊዜ የመስኖን ጠቀሜታ እየተገነዘበ መምጣቱን አስረድተዋል።

ባለፈው ጥቅምት በክልሉ 67 ወረዳዎች ለሚገኙ የግብርና ባለሙያዎችም አርሶ አደሩን እንዲያስተምሩ በመስኖ ቴክኖሎጂዎች አጠቃ ቀምና ጥገና ስልጠና መሰጠቱን አቶ ሃብቴ አብራርተዋል። የመስኖ ባለሙያዎችም በሁሉም ወረዳዎች እንዲመደቡ ተደርጓል ብለዋል።

አርሶ አደሮቹ በመስኖ በአመት ሁለትና ሶስት ጊዜ እንዲያመርቱ የክልሉ መንግስት ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝና የተሻለ የመስኖ ስራ የሚከናወንባቸውን ወረዳዎችና ቀበሌዎች በመለየት ተመክሮ የማስተላለፍ ስራ እየተሰራ እንደሆነ አመልክተዋል።

በክልሉ በመስኖ የሚለሙት ምርቶች ድንች፣ ቲማቲም፣ በቆሎ፣ አትክልት ፍራፍሬ፣ ቅመማ ቅመም ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን ከባለሙያው ገለፃ ለመረዳት ተችሏል።

## ትኩረት

# የቀሩትን ቀናት  ለውጤታማ ተግባር

ሚያዝያ ወር የሚካሄደው የአካባቢና የማሟያ ምርጫ ከ1997 አ.ም ምርጫ በሁለት መሰረታዊ ነገር ይለያል፡፡

አንደኛው መለያ፣ የአባል መሰረታችን ሰፋ ብሏል፡፡ በየጎጡ፣ በየቀበሌው፣ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በትምህርት ቤቶችና በከተሞች ድርጅታዊ መዋቅራችን ጠንካራ መሰረት ይዟል፡፡ በርካታ ግንባር ቀደም አባላትን አፍርተናል፡፡ እነዚህ አባላት፣ ሰርተው የሚያሰሩ፣ የድርጅትን ተልዕኮ በተሻለ ብቃትና ፍላጎት መፈፀም የሚችሉ ናቸው፡፡

ለምሳሌ በገጠር የሚገኙ የድርጅት መዋቅሮቻችን ጠንካራ የአመራር አቅም መፍጠር ጀምረዋል፡፡ አባላት በህዋሶቻቸውና በመሰረታዊ ድርጅቶቻቸው አማካይነት ፖለቲካዊ አቅማቸውን እየገነቡ ናቸው፡፡ በድርጅት አላማና ግብ ላይ የተሟላ ግልፅነት አላቸው፡፡ ስትራቴጂዎችን በተጨባጭ በመተርጎም ትርጉም ያለው ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ለተከታታይ አምስት አመታት ማስመዝገብ ችለዋል፡፡ ስለዚህ በገጠር የሚገኘው መዋቅራችን ጥራቱንና ብቃቱን እያጎለበተ ከመምጣቱ ባሻገር በግንባር ቀደምነት የሚወሱ በርካታ አባላትን ያሰባሰበ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ በአካባቢና በማሟያ ምርጫ የምናቀርባቸው አባሎቻችን የተሻለ ብቃትና አቅም ያላቸው፣ ህዝቡ በአርአያነት የሚቀበላቸውና የድርጅት ተልዕኮ መፈፀም የሚችሉ ናቸው፡፡

ሁለተኛው መለያ ደግሞ፣ በምርጫ 97፣ ህዝብ ያነሳውን ቅሬታ ለመፍታት ድርጅታችን የነደፋቸውን ስትራቴጂዎችና የማስፈፀሚያ ስልቶችን መፈፀም የሚችል አቅም መፍጠራችን ነው፡፡ እንደሚታወቀው በምርጫ 97 የተነሳው የጎላ ችግር የመልካም አስተዳደር ጉዳይ ነው፡፡ በመልካም አስተዳደር ረገድ ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልቶች ተነድፈው ምላሽ እየተገኘባቸው ይገኛሉ፡፡ ከአጭር ጊዜ አኳያ የተወሰደው የመፍትሄ አቅጣጫ ውጤታማነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከረጅም ጊዜ አንፃር የአሰራር ግልፅነትና ጥራትን በመፍጠር፣ በየደረጃው እንዲኖረውና አስፈፃሚ አካል የተሻለ አቅም እንዲኖረውና ህዝባዊና ድርጅታዊ ተልዕኮውን እንዲወጣ አድርጎ ማዘጋጀት ይጠይቃል፡፡

የአባላት ፖለቲካዊ አቅምን ለማሳደግ መጠነ ሰፊ የአቅም ግንባታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ እያንዳንዱ ሰው ተጠያቂ የሚሆንበት የአሰራር ስርአት ተዘርግቷል፡፡ ድርጅታዊ መዋቅሩ ስራውን የሚመራበት፣ የሚከታተልበትና አግባብ ያለው ድጋፍ የሚሰጥበት ሁኔታ ተመቻችቶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ከዚህ አንፃርም ቀላል የማይባል ውጤት ተገኝቶበታል፡፡

ከምርጫ 97 ወዲህ በልማት፣ በመልካም አስተዳደርና የህዝብ ጥያቄዎችን በማስተናገድ አንፃር ያከናወነው ተግባር ለአሁኑ ምርጫ የላቀ ትርጉም አለው፡፡ ይህ ምርጫ በርካታ ግንባር ቀደም አባላትን የምናሳትፍበት ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ተከታታይ ኢኮኖሚያዊ እድገት ባስመዘገብንበት፣ በከተሞች የሚታዩ መጠነ ሰፊ ችግሮችን ለመፍታት እንቅስቃሴ በጀመርንበት ወቅት ላይ የሚካሄድ ነው፡፡

ምርጫውን ለማሳካት አባላት ቀን ከሌት በመስራት ጅምሮቻችንን ዳር ለማድረስ መረባረብ ይጠበቅባቸዋል:: ይህ የሚሆነው ህዝቡ ህይወቱን የለወጠባቸው እምነቶች እንዳይነጠቁ ለማድረግ ብሎም ድርጅታችን ብአዴን/ኢህአዴግ ያስቀመጠውን አገራዊ ራዕይ ለማሳካት አስፈላጊ ስለሆነ ነው::

በገጠርም በከተማም የሚገኙ አባላት በምርጫው ላይ የሚያደርጉት ርብርብ ሁለት ገፅታ አለው:: አንደኛውና ዋነኛው ተግባር በቀሩት ጥቂት ቀናት ውስጥ አባሉ የምርጫውን መስፈርት የሚያሟሉ የቤተሰቡን አባላት በሙሉ ማስመዝገብ ይጠበቅበታል:: እዚህ ላይ ብቻም ማብቃት የለበትም:: ጎረቤቶቹን፣ መንደርተኞቹንና የስራ ባልደረቦቹን (እንደስምሪቱ) በመራጭነት እንዲመዘገቡ ማነሳሳት አለበት:: ከዚያም አልፎም ተርፎ ከምርጫ ምዝገባ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ውዥንብሮች ካሉ የማጥራት፣ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የመታገልና የማረም ድርሻም አለው::

አባላት በመራጮች ምዝገባ ላይ የሚያደርጉትን ጥረት ከተናጠል ተግባር ባሻገር የጋራ ማድረግ አለባቸው:: ለምሳሌ አባላቱ በጋራ የሚጠጧቸው ሰንበቴዎች፣ እቁቦች፣ እድሮችና የጋራ መድረኮች ካሉ እነዚህንም መጠቀም አስፈላጊ ነው::

በርካታ ህዝብ በመራጭነት ወጥቶ መመዝገቡ ለድርጅታችንም ሆነ ለመስመራችን ትርጉሙ የላቀ ነው:: አንዱና ዋነኛው ነጥብ ዴሞክራሲያዊ ስርአታችን እየጎለበተ መምጣቱን ያሳያል:: ሌላው የጀመርናቸው የልማትና የመልካም አስተዳደር ውጥኖችን ለማሳካት እንደ ግብአት ያገለግለናል:: ከምንም ነገር በላይ ግን በህዝብ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተውን ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመገንባት እና ለማጎልበት የላቀ ድርሻ አለው::

ሁለተኛው አባላት የሚጠብቃቸው ተግባር እጩዎችን የመለየት፣ የመገምገምና የማስተቸት ነው:: በአካባቢና በሟሟያ ምርጫ የምናቀርባቸው ዕጩዎች ከከዚህ ቀደሞቹ በብዙ መልኩ ይለያሉ:: ዋንኛ መለያቸው ግን ህዝቡ በግንባር ቀደምነታቸው የሚያውቃቸው፣ አቅማቸው የማያጠራጥር፣ በድርጅት ተልዕኮና ግብ ላይ ግልፅነት ያላቸው ናቸው:: እነዚህ ዕጩዎች አባላት በድርጅት መዋቅር አግባብ ባለው መልኩ መለየትና፤ አስተያየትም መስጠት ጀምረዋል:: በአንዳንድ የገጠር ቀበሌዎችና ወረዳዎች ህዝቡ በቀረቡ ዕጩዎች ላይ መተቸት ጀምሯል:: ድርጅት ያቀረባቸውን ዕጩዎች ከግንዛቤና ከልምዱ በመነሳት የሚጠቅሙትና የማይጠቅሙትን እየለየ ነው::

የዕጩ ዝግጅት የቀጣዮቹ ቀናት የርብርብ ማዕከል ነው:: ብዙ ዕጩዎችን መመልመል፣ ማዘጋጀትና በየደረጃው ማስተቸት አንድ አብይ ተግባር ነው:: በዕጩዎች ዝግጅት ላይ የሴቶችና የወጣቶች ተሳትፎ በተፈለገው መጠን እንዲሳካ አባላት ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል:: ጥራትና ብቃት ያለውን ዕጩን የመመልመል ስራ ያዝ ለቀቅ የሚደረግና በቅርብ የምናውቀው አባል ላይ ብቻ የታጠረ መሆን የለበትም:: በዚህ በኩል ሁሉም አባላት በህዋሶቻቸውና በመሰረታዊ ድርጅታቸው በኩል በንቃት ገብተው መሳተፍ አለባቸው:: አሁንም እየተሳተፉ ነው:: በዕጩ ዝግጅት ላይ ከዞን ጀምሮ እስከ ቀበሌ ድረስ ያለው አመራር ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል:: አመራሩ የመረጃ ልውውጥና የድጋፍ ስርአቱን የማጠናከር፣ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን የመገምገም፣ የመተንተንና ከትንተናው የጨበጠውን ሃሳብ በቅርበት በመመካከር ወደ ተግባር መተርጎም አለበት::

ይህ ማለት በምርጫ ስራው ላይ በቀሩት ጥቂት ቀናት መራጮችን በብዛት እንዲመዘገቡ ማድረግና ብቃትና ጥራት ያላቸውን ዕጩዎች በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ የሚታዩ ዝንባሌዎችን፣ አመለካከቶችና

ተግባሮችን ለይቶ ማወቅ፣ ምንጫቸውን መፈተሽ፣ ከሚገኘው ውጤት በመነሳት ተገቢ ትግል ማድረግ ማለት ነው።

በዕጩ ዝግጅት ላይ የታዩ አንዳንድ አዎንታዊና አሉታዊ ነገሮችን በምሳሌ አንስተን እንይ። የሰሜን ወሎ ዞን 91200 የቀበሌ ዕጩዎችን በአባላት ቀጥተኛ ተሳትፎ መልምሎ ማዘጋጀት ጀምሯል። የሴቶችን ተሳትፎም ከሞላ ጎደል ከ30 እስከ 40 በመቶ አድርሷል። በድርጅት ደረጃ የተመለመሉ ዕጩዎችን በህዝብ ማስገምገም ጀምሯል። የዞን አመራሩ ይህንን ተግባር ወረዳዎችን እየተከፋፈለ በመምራት ላይ ሲሆን ተግባሩን መነሻ ያደረገ ግምገማና የመረጃ ልውውጥ አለው። በአንፃሩ ምዕራብ ጎጃም ዞንን ደግሞ ስንመለከት ከዕጩ ዝግጅት አንፃር አንዳንድ ቀበሌዎች ላይ አባላት አልተሳተፉም። የቀበሌ አመራር ብቻ የመለመለበት ሁኔታ ተስተውሏል። አመራሩ ስራውን አቀናጅቶ በመምራት ረገድ የሁኔታ ግምገማና የመረጃ ልውውጥ ላይ ክፍተት ይታይበታል። የሴቶችና የወጣቶች ተሳትፎም አነስተኛ ነው። የተመለመሉ ዕጩዎችን በህዝብ ለማስተቸት የሚያስችል የተሟላ ዕቅድም አልተሰራም። በንፅፅር ማየት እንደሚቻለው በዕጩ ዝግጅትም መራጮችን ለምዝገባ የማነሳሳት ስራ ላይ አመራሩ ትኩረት በሰጠበት አካባቢ ውጤታማ ሲሆን፣ የአመራሩ ትኩረት ባነሰበት ደግሞ ስራው የመዝረክረክ ዕጣ ሲያጋጥመው ይስተዋላል።

መግቢያችን ላይ እንዳነሳነው የአካባቢና የማሟያ ምርጫ፣ ከ97ቱ ምርጫ በበርካታ ነገሩ ይለያል። ዴሞክራሲያዊ ስርአታችን የማጠናከር፣ የዴሞክራሲ ባህሉን የማስረጽ፣ አገራዊ ራዕያችን የበለጠ ለማሳካት አስተማማኝ መሰረት የመጣልና የድርጅታችንን መዋቅር በተሻለ አቅምና ጥረት ባላቸው አባላት እየገነባን መሄዳችንን የምናረጋግጥበት ነው። የተጀመረውን የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራ የማስቀጠሉ ዋነኛ ስራ የሚያርፈው በታችኛው መዋቅር ላይ በመሆኑም አሁን የሚካሄደው ምርጫ ፋይዳው የላቀ ነው። አባላት ተልዕኳቸውን የመፈፀም አቅማቸውን ይበልጥ የሚያረጋግጡበትም ይሆናል። ስለዚህ በየደረጃው ጠንክሮ መስራት ያስፈልጋል። በጥቅሉ ከፊት ለፊታችን ሶስት አበይት ተግባራት ይጠብቁናል።

- የዕጩ ዝግጅታችን የሴቶችና የወጣቶችን ተሳትፎ ያረጋገጠ መሆን ይገባዋል። አባላት ከዚህ አንፃር በያሉበት መዋቅር ያልተሟላ ስራ ካለ ለማሟላት መስራት አለባቸው።

- የተዘጋጁ ዕጩዎች በአባላት ቀጥተኛ ተሳትፎ የተመረጡ መሆናቸውንና አለመሆናቸው ማረጋገጥ፣ (አባላት ከዚህ አንፃር የሰላ ትግል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል)

- የተዘጋጁ ዕጩዎችን ፈጥኖ በህዝብ ማስተቸት መጀመር ያስፈልጋል። የህዝብ መድረኮች በተጀመሩባቸው አካባቢዎች የተገኙ ልምዶችን ፈጥኖ በመቀመር ወደ ሌላው ማስተላለፍ ያስፈልጋል።

ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት በቀጣዮቹ 10 እና 15 ቀናት ውስጥ ለመወጣት ሁሉም በየደረጃው በግልና በጋራ ሃላፊነቱን ታሳቢ አድርጎ የድርሻውን ያንሳ።